# Infodossier Amharisch



የኮቪድ-19 ክትባት

የተሻሻለበት ቀን፡ 27.10.2021

1 / 1

ራሳችንን የምንጠብቅበት መንገድ ይህ ነው.

## የኮቪድ-19 ክትባት ለመከተብ ጥሩ ምክንያቶች

**የኮቪድ-19 ክትባትን ለምን ይከተባሉ? ለዚህ የሚሆኑ በርካታ ጥሩ ምክንያቶች አሉ። የኮቪድ-19 ክትባት የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመዋጋት በጣም ጠቃሚ ነው። እንደ ንጽህና እና የባህርይ ደንቦች የመሳሰሉትን ሌሎች እርምጃዎች የሚያጠናክር ነው። ክትባት ከሕመም በተለይም ከባድ ከሚባሉ በሽታዎች የሚጠብቀን ነው። ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚኖሩ ተጨማሪ ሰዎች ክትባቱን በወሰዱ ቁጥር፣ የሌሎች እርምጃዎች አስፈላጊነት ይቀንሳል።**

### እራስዎን ከከባድ በሽታ ይከላከሉ።

የኮቪድ 19 በሽታ በተለይም ዕድሜያቸው ለገፋ ሰዎችና ስር የሰደደ በሽታ ላለባቸው ሰዎች በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ወጣቶችና ጤናማ ሰዎች በኮሮናቫይረስ ሲያዙ የሚያሳዩት ምልክት መጠነኛ ነው ወይም ምንም ምልክት አያሳዩም። ነገር ግን፣ እነርሱም በበሽታው ከባድ ሁኔታ ሊጠቁ ይችላሉ። ክትባት ከኮቪድ-19 በሽታ በተለይም ከከባድ ሕመም ሊከላከለዎት ይችላል። በከፍተኛ ክትትል ክፍል ውስጥ ተኝተው ከሚገኙ የኮቪድ ታማሚዎች መካከል ከ 90% በላይ የሚሆኑት ክትባት ያልተከተቡ ናቸው። ስዊዘርላንድ ውስጥ የሚሰጡት ክትባቶች አስተማማኝና ከኮቪድ-19 በሽታ በጣም ጥሩ ከለላ ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው። አንድ ክትባት ስዊዘርላንድ ውስጥ ፈቃድ ሊሰጠውና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው ጠቀሜታዎቹ ከስጋቶቹ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ልቀው ሲገኙ ነው። እስከዛሬ ድረስ እነዚህን ክትባቶች በተመለከተ ያለው ተሞክሮም ይህንኑ የሚያሳይ ነው።

### ኮቪድ-19 የሚያስከትላቸውን ጉዳቶች ማስቀረት

በበሽታው ከተያዙ በኋላ፣ ዘለቄታዊ የሆኑ የጤና ችግሮች (ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ኮቪድ) ሊከሰቱ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡ ከባድ እንቅስቃሴ

### ለጤና ባለሙያዎች ድጋፍ ያድርጉ

ወረርሽኙ በጤና እንክብካቤ ሰራተኞችና በጤና እንክብካቤ ስርዓቱ ላይ ጊዜያዊ ጫና አሳድሯል። ክትባቱ በሚሰጥዎት መከላከያ አማካይነት፣ ለከባድ የኮቪድ-19 በሽታ ሕክምና ማግኘት አያስፈልግዎትም። ይህን በማድረግዎ፣ በጤና እንክብካቤ ስርዓቱ ላይ የሚደርሰውን ጫና ለማቃለል ያግዛሉ። ለሌሎች ሕመሞችና ድንገተኛ የጤና ችግሮች የሚሰጡ ሕክምናዎች ግን አሁንም ይሰጣሉ።

### በዙሪያዎ ያሉ ሰዎችን መጠበቅ

ክትባቱን ከወሰዱ፣ እርስዎ በበሽታው የመያዝዎና ሌሎችንም የመበከል ስጋት በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል። ምንም እንኳን ክትባቱ የበሽታውን የመተላለፍ ዕድል ሙሉ በሙሉ ባይከላከልም፣ በተለይ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎችን መጠበቅ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ክትባቱ ውጤት የማያስገኝላቸውና የተዳከመ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ያላቸው ሰዎች። እርስዎ መከተብዎ በጤና ምክንያት መከተብ ያልቻሉ ሰዎችና መከተብ የማይችሉ ሕጻናትን ከበሽታ ይከላከላል። የተከተቡ ሰዎች ቁጥር ሲጨምር፣ ራሳቸው በኮቪድ-19 የሚያዙና ሌሎች ሰዎችንም የሚበክሉ ሰዎች ቁጥር ይቀንሳል።

የኮቪድ-19 ክትባት ለመከተብ ጥሩ ምክንያቶች

Shortlink: https://bit.ly/migesplus-guteGruende_amh
………………………………
Merkblatt: Gute Gründe für die Impfung




በስዊዘርላንድ ውስጥ ስለ ኮሮናቪይረስ ክትባት ያለዎት አስተያየት ምንድነው?

Shortlink: https://bit.ly/migesplus-testimonial_amh
………………………………
Video mit Testimonial zur Impfung 2021, diaspora-tv




ክትባቱ የፋርማሱ ኢንዱስትሪ ብቻ የሚያውቃቸውን ሌሎችወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን ያስከትላል

Shortlink: https://bit.ly/migesplus-impfmythosKrankheiten_amh
………………………………
Video Impfmythen Krankheiten, diaspora-tv




የኮሮና ቫይረስ ክትባት መከተብ ያለብዎት 10 ምክንያቶች

Shortlink: https://bit.ly/migesplus-zehnGruende_amh
………………………………
10 Gründe, warum Sie sich gegen das Coronavirus impfen lassen sollten.